# መሠረታዊ
# የክርስትና
# ትምህርት

# ክፍል አንድ

## የመዳን ትምህርት

### ⇨ የወደቀው መልአክ (ሰይጣን) አፈጣጠርና አወዳደቅ

- ☞ **ሰይጣን፡-** የሂብሪው ቃል ሲሆን ትርጉሙም "አሰናካይ" ጠላት እንቅፋት የሚያኖር ማለት ነው፡፡
- ☞ **ዲያብሎስ፡-** የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ከሳሽ ማለት ነው፡፡

**ለምን ተፈጠረ?**

1. እግዚአብሔርን ለማመስገን ተፈጠረ **ሕዝ 28:13**
2. የእግዚአብሔርን ክብር ለመጋረድ የተቀባ (የተሾመ) ነበረ **ሕዝ 28:14**
3. ውበቱም የተፈፀመ መደምደምያ ነበር **ሕዝ 28:12**

**ለምን ወደቀ?**

1. በውበቱ ምክንያት ኩራ (ትዕቢት) **ሕዝ 28:17**
2. በልዑል እግዚአብሔር መመሰል (መሆን) ፈለገ **ኢሳ 14:12**

**የኃጢአቱ ውጤት**

1. ከነተከታዮቹ ወደምድር ተጣለ **ሕዝ 28:17**
2. ወደፊት ደግሞ ወደጨለማው ጉድጓድ ወደ እሳት ባህር ውስጥ ይጣላል **ኢሳ 14:15, ማቴ 25:41, 2ጴጥ 2:4**

### ✸ የሰው አፈጣጠርና - አወዳደቅ

- ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ ተፈጠረ **ዘፍ 1:26**
- እግዚአብሔር ከምድር አፈር አበጀው **ዘፍ 2:7**
- ሰው ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ **ዘፍ 2:7**
- አካባቢውን ሁሉ እንዲገዛ ተፈጠረ **ዘፍ 1:26**
- ገነትን ይጠብቃት ያበጃትም ዘንድ በዚያ አኖረው **ዘፍ 2:15**
- የሚመቸውን ረዳት ፈጠረለት **ዘፍ 2:18-25**
- ከዕውቀት ዛፍ እንዳይበላ አዘዘው **ዘፍ 2:16**

✸ **ውድቀት**

- ሰይጣን/እባብ/ ሴቲቱን አታለላት **ዘፍ 3:1-7, 1ጢሞ 2:14**
- ባልየው የሚስቱን ቃል በመስማት ተላለፈ **ዘፍ 3:6, 3:17**

✸ **ምክንያት** - እንደእግዚአብሔር ለመሆን በመፈለግ **ዘፍ 3:5**
- ከፈጣሪ ይልቅ የፍጥረትን ድምጽ ወይም ቃል በመስማት (ሴቲቱ የሰይጣንን፣ ወንዱ የሚስቱን ቃል አደመጡ)

- ዛፉ ለመብላት ያማረ → 1. የሥጋ ምኞት
- ለዓይንም እንደሚያስጐመጅ → 2. የዓይን አምሮት
- ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች → 3. የኑሮ ትምክህት

**ዘፍ 3:6** **1ዮሐ 2:16 (የ1980 ትርጉም)**

✓ እነዚህ ሦስቱ የኃጢአት መግቢያ መንገዶች ናቸው:: ሰይጣን ሰውን ፈትኖ የሚጥለው በነዚህ 3 መንገዶች ተጠቅሞ ነው:: ጌታ ኢየሱስ የተፈተነበትን ታሪክ ከማቴዎስ 4:1-10 በማንበብ እነዚህን 3 ነጥቦች ለማገናኘት ሞክር::

✸ **የኃጢአት ውጤቶች በሰው ላይ**

1. እራቁትነት /ጉስቁልና/ ነውር በሰው ላይ መጣ **ዘፍ 3:7**
2. ፍርሃት /ሽሽት/ ተጀመረ **ዘፍ 3:8-10**
3. እርግማን መጣ **ዘፍ 3:16-21**
4. ከገነት ተባረሩ **ዘፍ 3:22-24**
5. ሰው ሰውን መበደል ጀመረ **ዘፍ 4:1-8**
6. የሰው የልቡ አሳብ ክፉ ሆነ **ዘፍ 6:5**

## ✸ ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ሆነ

- ተወልዶ እስኪሞት ሕግን በመጠበቅ ጸንቶ የሚኖር ማንም ሰው የለም **ሮሜ 3:20** ስለዚህ ሰው ሁሉ ሕግን በመተላለፍ የተነሳ የተረገመ ሆነ **ገላ:310**
- ሰው ሕግን ሁሉ ቢጠብቅ ነገር ግን በአንዲቱ (ለምሳሌ አትመኝ) ቢስት በሁሉ ተጠያቂ በደለኛ ይሆናል:: **ያዕ 2:10**

ስለዚህ ሰው በዕድሜ ዘመኑ አንዴ ቢስት እንኳ መጽደቅ አይችልም ነበር:: ከዚህም የተነሳ በሰው ግምት ጻድቅ የሚባሉ እንኳ ሁሉን በሚያውቀው በአምላክ ፊት ኃጢአተኞች ናቸው:: **ሮሜ 3:23, ሮሜ 5:12, መክ 7:20**

- ✱ ሰው <u>በእግዚአብሔር ፊት ፃድቅ</u> ሊሆን አይችልም:: **ኢዮ 4:17, 9:2, ሮሜ 3:20**
- ✱ አንድም ስንኳ ፃድቅ የለም:: **መዝ(14):2, ሮሜ 3:11**
- ✱ ፃድቃን የሚባሉ እንኳ ኃጢአት ያደርጋሉ:: **መክ 7:20**
- ✱ ጽድቃችን እንኳ በፊቱ በቂ አይደለም:: **ኢሳ 64:6**
- ✱ ሕግን በመፈጸም <u>በእግዚአብሔር ፊት</u> መጽደቅ አይቻልም:: **ሮሜ 3:20, ገላ 2:16,21, ኤፌ 2:8**
- ✱ በሰው ልጆች መካከል የጽድቅ ልዩነት የለም:: **ሮሜ 3:22**
- ✱ ፀጋው በእምነት ያጸድቃል:: **ሮሜ 3:22-25**

<u>**ማስታወሻ**</u> (በተጨማሪ "ሕግና ፀጋ" የሚለውን ትምህርት ተመልከት(ቺ))

## <u>አምላክ ሰውን ለማዳን ያዘጋጀው መፍትሔ</u>

- ማንም ሰው ራሱን ማዳን በምንም መንገድ አይችልምና እግዚአብሔር ራሱ ሰውን የሚያድንበት መፍትሔ አዘጋጀ::
  - ልጁን መድኃኒት እንዲሆን ላከው **1ዮሐ 4:14**
  - አስቀድሞ እግዚአብሔር ልጁን ከመላኩ በፊት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ስለሚመጣው መድኃኒት በምሳሌ ያሳይ ነበር::

**ለምሳሌ:-** አዳም እርቃኑን ለመሸፈን ሲል በራሱ እጅ ቅጠል ሰፍቶ አገለደመ:: እግዚአብሔር ግን የአዳምን ገመና ራሱ እግዚአብሔር ባዘጋጀው ቁርበት ሸፈነለት:: (ይህም የአዳምን የኃጢአት ውጤት ለመሸፈን አንድ እንስሳ ሞቷል ማለት ነው:: እርሱም የኢየሱስ ምሳሌ ነበር):: **ዘፍ 3:2**

- ከሴቲቱ የሚወለደው የእባቡን ራስ እንደሚቀጠቅጥ አምላክ ትንቢት ተናገረ **ዘፍ 3:5**
- ለእስራኤል ልጆች ለኃጢአት ስለሚሰዋው በግ በምሳሌ አስተማራቸው:: **ዘሌ 4**

**ለምሳሌ:-** በብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ በጥላና ምሳሌ መልክ ጌታ ኢየሱስን በብዙ መቶዎች በሚቆጠር ሥፍራዎች /ጥቅሶች/ ውስጥ እናገኘዋለን:: **በብሉይ የተገለጡ ነገሮች በሙሉ ጥላ ሲሆኑ አካሉ ግን የክርስቶስ** ነው:: **ቈላ 2:16**

### የዘሌዋውያን ምዕራፍ 4 በግ ምሳሌነትና ትርጉሙ

- አንድ ሰው አንዲቱን ትዕዛዝ ቢተላለፍ ለኃጢአቱ መስዋዕት የሚሆን ነውር የሌለበት ወይፈን፣ በግ ወይም ፍየል ይዞ ይቀርባል:: እጁንም በወይፈኑ ራስ ላይ ጭኖ ኃጢአቱን ለእግዚአብሔር በመናዘዝ ያሸክመዋል:: ወይፈኑንም ያርደዋል:: ካህኑም ደሙን ወስዶ በመገናኛው ድንኳን ፊት 7 ጊዜ ይረጨዋል::

**በአዲስ ኪዳን የዚህ ምሳሌ ትርጉም**

- ነውር የሌለበት በግ ኢየሱስ ነው:: **ዮሐ 1:24, ዕብ 7:26**
- ጌታ ኢየሱስ ራሱን ስለእኛ ኃጢአት አቀረበ:: **ዕብ 7:27, 10:12**
- ኃጢአታችንን ሁሉ ተሸከመ **1ጴጥ 2:24, ኢሳ 53:6,12**
- የእግዚአብሔር በግ ለኃጢአታችን ታረደ (ሞተ) **1ቆሮ 5:7, ራዕ 5:9**

**የብሉይ ኪዳን የእንስሳት መስዋዕት ለምን ቀረ?**

- ጌታ ኢየሱስ እስኪሞት ድረስ በምሳሌነት የተሰጠ ነበረና **ዕብ 9:10**
- የፍየሎችና የበጐች ደም ኃጢአትን ሊያስወግድ አይችልምና:: **ዕብ 10:4, 11, 9:12**
- ሥርዓቱ የተሰጠው ለዓለም ሕዝብ ሳይሆን ለእሥራኤል ብቻ ነበረ **ዘሌ 4:2**

## መፍትሔ ከአምላካችን ዘንድ

ሰው በማናቸውም ሁኔታ፣ በመልካም ሥራ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ፍፁም ሊሆን ወይም ሊጸድቅ አልቻለምና እግዚአብሔር ራሱ ዓለም ሳይፈጠር በፊት ለሚጠፋው የሰው ልጅ ያቀደውን የመዳን መንገድ ገለጠው:: ይህም መንገድ “**ፀጋ**” ይባላል:: ፀጋ ማለት “**ለማይገባው ማንነት እንዲሁ የሚሰጥ**” ማለት ነው:: ይህም የሰውየውን ጥሩነት በማየት ሳይሆን እንዲሁ ከሰጪው ደግነት የተነሣ የሚሰጥ ነፃ ስጦታ ነው:: ከሰውየውም የሚጠበቀው **በቸርነት** የተሰጠውን **ፀጋ** በእምነት መቀበል ብቻ ነው::

## የፀጋው አሠራር

- እግዚአብሔር ቃል ሥጋ ሆነ **ዮሐ 1:14**
- እግዚአብሔር ቃሉን (ልጁን) የዓለም መድኃኒት ሊሆን ላከው **1ዮሐ 4:14**
- የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ **ማቴ 16:16** ሕግን በሙሉ ፈጸመ:: ከቶም ኃጢአትን አላደረገም **ዕብ 4:15, ዕብ 2:14-18** እግዚአብሔር ልጁን በእኛ ምትክ እንዲሞት፣ እኛ ደግሞ በእርሱ ጽድቅ እንዲሁ እንድንጸድቅ አደረገ::

| ***የዓለም ሕዝብ*** | ***ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ*** |
|---|---|
| - ሁሉም ኃጢአትን አድርገዋል<br>- ሕግን በመጠበቅ ሊጸድቁ ስለማይችሉ ርጉም ሆኑ:: | - የሰውን ሥጋ ለብሶም ኃጢአት አያውቀውም<br>- ሕግን ሁሉ ፈጽሟል |

## *እርሱ ስለእኛ ፈንታ*

*ኃጢአት ሆነ* **2ቆሮ 5:21**

*ርግማን ሆነ* **ገላ 3:13**

በእኛ ላይ ያለውን ኃጢአታችንን በመሸከም ኃጢአት የሚያመጣውንም ርግማን እና ሞት ለራሱ በመውሰድ እኛ ነፃ እንድንሆን አደረገ። ኢየሱስ የዓለምን ኃጢአት ሁሉ ተሸክሟል። ነገር ግን ሰው ለመዳን ከፈለገ በኢየሱስ ሥራ ብቻ እንደሚጸድቅ ማመን አለበት።

አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ሲያምን ምን ይሆናል?

በኢየሱስ ያመነ ሰው:-

1. የዘለዓለም ሕይወት አለው /አይጠፋም/ **ዮሐ 3:16,18**
2. ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግሯል ወደፍርድ አይመጣም **ዮሐ 5:24**
3. ኩነኔ የለበትም **ሮሜ 8:1**
4. በሕግ ጉዳይ አይጠየቅም **ሮሜ 6:14**
5. ከኃጢአቱ ታጥቧል፣ ጸድቋል፣ ተቀድሷል **1ቆሮ 6:11**
6. ዳግመኛ ተወልዷል **ዮሐ 1:12**
7. የእግዚአብሔር ልጅ ሆኗል **ሮሜ 8:14-17, ገላ 4:6**
8. አዲስ ፍጥረት ሆኗል **2ቆሮ 5:17**
9. ኃጢአቱ ተሰርዮለታል **1ዮሐ 2:12, ሮሜ 4:5-8**
10. የዘለዓለም ፍፁም ሆኗል **ዕብ 10:14**
11. ያለምንም ሥራ በእምነት ብቻ ጸድቋል **ኤፌ 2:8**
12. የፀጋ ስጦታ ተሰጥቶታል **1ቆሮ 12:4-11, ቁ 27-28**
13. በመንፈስ ቅዱስ ታትሟል **ኤፌ 1:13**
14. መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ገብቶበታል **ዮሐ 7:38, 14:15-17**
15. በአብ ቀኝ ተቀምጧል **ኤፌ 2:4-8 ወዘተ...**

## *ለመዳን*

### *ጌታ ኢየሱስን ብቻ ለምን መረጥን?*

**ምክንያቱም:-**

- እርሱ ብቻ አዳኝ ስለሆነ **ኢሳ 43:11, ሐዋ 4:12**
- ለኃጢአታችን የሞተው እርሱ ብቻ ስለሆነ **ዮሐ 3:15, 1ቆሮ 15:3**
- ከኃጢአት የሚያነፃው የእርሱ ደም ብቻ ስለሆነ **1ዮሐ 1:17**
- በእርሱ ብቻ ወደ አብ ስለሚደረስ **ዮሐ 14:5-6, ኤፌ 2:18**
- ሕይወት እርሱ ብቻ ስለሆነ ዮሐ 14:6

# ***ክፍል ሁለት***

## ***የውኃ ጥምቀት***

**ጥምቀት**:- በግሪክ "ባፕቲዞ" ሲባል የቃሉ ትርጉም "ማስጠም" ማለት ነው::

"**Baptism**":- Immersion - አንድ ነገር ሙሉ በሙሉ በውኃ ሲሸፈን (ሲሰወር) ማለት ነው::

- ቤተክርስቲያን አህዛብን ሁሉ እያስተማረች እንድታጠምቅ በጌታ ታዛለች:: **ማቴ 28:19, ማር 16:15**
- የዘለዓለም ሕይወት ፈጽሞ በጥምቀት አይገኝም:: ሰው ለመጠመቅ የግድ በቅድሚያ በኢየሱስ በማመን መዳን ይኖርበታል::

## ***በውኃ የመቀበሩ (የመጠመቁ) ትርጉም ምንድ ነው?***

**ሀ.** ከኢየሱስ ጋር መቀበር ነው:: **ሮሜ 6:4, ቈላ 2:12**

አማኙ ከጌታ ኢየሱስ ጋር አብሮ ለመቀበር እንኳ የተስማማ (የተባበረ) መሆኑን ይገልጽበታል:: ይህም ከውኃው በሚጠልቅበት ቅጽበት ይገለጣል::

**ለ.** ከኢየሱስ ትንሣኤ ጋር መተባበሩን ያሳያል:: **ሮሜ 6:4-5**

ይህም ከውኃው በሚወጣበት ቅጽበት ይገለፃል::

ጌታ ኢየሱስ በመቃብር ውስጥ　　　　አማኙ በጥምቀት አብሮ ሲቀበር

**ሐ.** ከዚያ በኋላ በአዲስ ሕይወት መመላለስ ይገባል:: **ሮሜ 6:8,4,11**

## **ከጌታ ኢየሱስ ጥምቀት መማር ማቴ 3:1-17**

- ዮሐንስ የንስሐ ጥምቀት ያጠምቅ ነበር:: **ማቴ 3:11**
- ሰዎች ሁሉ ኃጢአታቸውን እየተናዘዙ ይጠመቁ ነበር **ማቴ 3:5**
- ያን ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ሊጠመቅ ከገሊላ - ዮርዳኖስ /60 miles ተጉዞ መጣ::/

**<u>አስታውስ(ሽ)</u>** ጌታ ኢየሱስ ፈጽሞ ኃጢአትን አያውቅም::

- ነገር ግን ኃጢአተኞች የሚጠመቁትን ጥምቀት ሊጠመቅ መጣ:: **ማቴ 3:13**
- ዮሐንስም ይከለክለው ጀመር /**ማቴ 3:14**/ ዮሐንስ ፈጽሞ ትክክል ነበር:: ምክንያቱም ኢየሱስ ኃጢአት የለበትምና::
- ለኢየሱስ ቢጠመቅ የሚጨምርለት፣ ባይጠመቅ የሚጐድልበት ነገር አልነበረም::
- ነገር ግን ጌታ ኢየሱስ አጥጋቢ ምክንያት ነበረው::

***"እንግዲህ ፍቀድልኝ፣ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ ልንፈጽም ይገባናልና" ማቴ 3:15 አለው::***

**<u>አስታውስ(ሽ)</u>** ደህንነት ወይም የዘለዓለም ሕይወት የሚገኘው በጌታ ኢየሱስ ለኃጢአታችን መሞትና መነሳት እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን **በማመን** ብቻ ነው::

- ሰው አምኖ ከዳነ በኋላ ጊዜ ካለው ግን የውኃ ጥምቀት በመውሰድ ከጌታ ጋር በመቃብር እንኳ ለመተባበር ፈቃደኛ መሆኑን ማሳየት ይኖርበታል::

## እነማን ይጠመቁ?

- አንድ ሰው የውኃ ጥምቀትን ከመውሰዱ በፊት ሊያሟላቸው የሚያስፈልጉ ሦስት ቅድመ ሁኔታዎች አሉ:: ወይም ደግሞ የውኃ ጥምቀትን የሚቀድሙ 3 ነገሮች አሉ::
    1. የወንጌል ትምህርት  2. እምነት  3. ንስሐ/መናዘዝ
- ሐዋርያት እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች ያላሟሉ ሰዎችን ፈጽሞ አያጠምቁም ነበር::

**ለምሳሌ ጴጥሮስ ሐዋ 2:14-47**

1. ጴጥሮስ ወንጌልን ሰበከ **ሐዋ 2:14-36**
2. ሰዎቹ ልባቸው ተነካ (አመኑ) **ሐዋ 2:37**
3. ንስሐ እንዲገቡ (ኢየሱስን እንዲናዘዙ) ታዘዙ **ሐዋ 2:38**
4. ተጠመቁ **ሐዋ 2:41**

**<u>አስታውስ(ሽ)</u>**: ቃሉን የተቀበሉ (ብቻ) ተጠመቁ **ሐዋ 2:41**

ሕፃናት ወንጌል አይሰበክላቸውም እነርሱም፣ ተረድተውት ልባቸው አይነካም፣ እንዲሁም ንስሐ ግቡ የሚባሉበትም ሁኔታ የለም::

## ዲያቆን ፊልጶስ ሐዋ 8:26-40

1. ስለኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት ቁ 35
2. ሰውየው ለመጠመቅ እንኳ ዝግጁ ሆነ ቁ 36
   ፊልጶስ ግን መጠመቅ ትችላለህ አላለውም:: ይልቅስ በፍጹም ልብህ ብታምን ተፈቅዶአል አለው::
3. ተናዘዘ ቁ 38
4. ተጠመቀ ቁ 38, 39

✓ በአጠቃላይ ጥምቀት አማኙ ኢየሱስን በማመን ብቻ የዘለዓለምን ሕይወት ተስፋ ከተቀበለ በኋላ የቤተክርስቲያን /የአጥቢያ/ አባል ለመሆንና፣ እንደሌሎች ወንድሞቹ ሁሉ ለኃጢአት መሞቱን እና ከጌታ ኢየሱስ ጋር መቀበሩን፣ መነሣቱን፣ እንዲሁም በአዲስ ሕይወት ለመመላለስ መወሰኑን የሚያሳይበት ነው::

# *ክፍል ሦስት*

## *የጌታ ራት*

"... ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንስቶ አመሰገነ ቈርሶም:- እንካችሁ ብሉ ይህ ስለእናንተ የሚሆን *ሥጋዬ* ነው፣ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ:: እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ አንሥቶ ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው:: በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት" አለ:: **1ቆሮ 11:23-26**

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ አምነው ለዳኑት አማኞች ሁሉ ከጥምቀት ቀጥሎ ይፈጽሙት ዘንድ በቋሚነት ከሰጣቸው ሥርዓቶች ሁለተኛው ነው:: የጌታ ራት ለሁሉም አማኞች የጌታን ሞት ያስቡበት ዘንድ የተሰጠ ቅዱስና ክቡር ሥርዓት ነው::

### *ስያሜዎች:-*

1. የጌታ ራት 1ቆሮ 11:20 (የቆሮንቶስ ሰዎች ግን ሳቱ)
2. የጌታ ማዕድ 1ቆሮ 10:21 (ከሌላ ማዕድ መካፈል አይቻልም)
3. እንጀራውን መቁረስ ሐዋ 2:42 (ከተጠመቁ በኋላ ይተጉ ነበር)

### ዓላማው:-

**1. የጌታ ሥጋና፣ በደሙ የተፈጸመው የአዲስ ኪዳን መታሰቢያ**

ጌታ ኢየሱስ ለዓለም ሁሉ ኃጢአት ተላልፎ ከመሰጠቱና ኃጢአታችንን ተሸክሞ ከመሞቱ በፊት የፋሲካን ራት በሚበሉበት ምሽት ላይ የሚበላውን ቂጣ እንጀራ አንስቶ በመባረክ ለደቀመዛሙርቱ እንዲካፈሉት ቆርሶ ሰጣቸው:: ነገ በመስቀል ላይ የሚሰቀለውንና የሚሞተውን ቅዱስ ሥጋውን በዚያ ቂጣ እንጀራ አማካይነት እንዲያስቡት ለመታሰቢያነት ሰጣቸው:: እንዲሁም ከእራት በኋላ ደግሞ ለዓለም ኃጢአት የሚፈሰውን ክቡር እና ንጹህ ደሙን እንዲሁም በዚህም ደም የተፈጸመውን አዲስ ኪዳን ያስታውሱበት ዘንድ በጽዋ ውስጥ የተሞላውን ወይን ጠጅ ባርኮና አመስግኖ ሰጣቸው:: ይህም ከዚያን ሌሊት ጀምሮ (ለቤተክርስቲያን) እርሱ እስኪመጣ ድረስ የጌታን ሞት የምናስብበትና ያን በእንጨት ላይ የዋለ ሥጋውንና የፈሰሰውን የሚያነፃ ደሙን የምናስታውስበት መታሰቢያ ነው::

ይህ ማለት ቂጣ እንጀራው አሁን በአብ ቀኝ ያለውን እውነተኛ ሥጋውን ያስታውሰናል እንጂ ራሱ ቂጣው ሥጋ ነው ወይም ይሆናል ማለት አይደለም:: እንዲሁም ጽዋው የዛሬ 2000 ዓመት ለዓለም ሁሉ ኃጢአት የፈሰሰውን ደሙን ያስታውሰናል እንጂ በራሱ ወይን ጠጁ ደም ነው ማለት አይደለም:: ቂጣውንና የወይን ጠጁን ተለውጦ ሥጋ ይሆናል፣ ደም ይሆናል ማለት እጅግ የተሳሳተ መረዳት ሲሆን በአብ ቀኝ የተቀመጠውንም ያን ክቡር ኢየሱስ ማክፋፋት ነው:: እርሱ ሁልጊዜ ይሠዋል እንደማለት ነው:: **ዕብ 9:26**

**ምሳሌያዊ ማብራሪያ**:-ለምሳሌ አንድ ወንድማችን ፎቶግራፉን ቢሰጠንና ይህ እኔ ነኝ ይህን ለማስታወሻ ውሰዱት ቢለን ፎቶግራፉ በራሱ ግን ልጁ ራሱ አለመሆኑን እናውቃለን:: ነገር ግን ለወንድማችን ባለን አክብሮትና ፍቅር መጠን ለፎቶግራፉ ያለን ክብር ይወሰናል:: ለፎቶግራፉ ያለን ከበሬታ ከጠፋ ለወንድማችን ያለንን ጥላቻ ገለጽን ማለት ነው::

**2. የጌታን መከራና ሞት ማስታወሻ**

"ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት" **ሉቃ 22:20** በዚህ መሠረት ቤተክርስቲያን ቂጣ እንጀራ እና የወይን ጠጅ በማዘጋጀት የጌታን መከራና ሞት በማሰብ በዚህም ለእርሷ የተደረገላትን መዳን እያሰበች ጌታን ታመሰግንበታለች:: እንጀራውንም በመብላት ጽዋውንም በመጠጣት የጌታን ሞት እርሱ እስኪመጣ ድረስ ትናገራለች:: **1ቆሮ 11:26**

**3. የቤተክርስቲያንን አንድነት መግለጫ**

አንድ እንጀራ ስለሆነ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋነን ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና **1ቆሮ 10:17** እግዚአብሔርና ቃሉ የሚያውቁት አንዲት ቤተክርስቲያን እንዳለች ብቻ ነው:: በጌታ ኢየሱስ ያመኑና የዳኑ በሙሉ አንድ ላይ አንዲት ቤተክርስቲያን ተብለው ይጠራሉ:: አማኞች በቁጥር ብዙ ቢሆኑም ስንኳ ነገር ግን አንድ አካል /ቤተክርስቲያን/ ናቸው:: ይህን የሚገልጹትም በአካል ምንም ብዙዎች ቢመስሉም ግን አንድ ሥጋ መሆናቸውን አንዱን ቂጣ እንጀራ በመቁረስ ያረጋግጣሉ:: **1ቆሮ 12:12-28**

## እነማን ይካፈሉ? ይቁረሱ?

የጌታ ራት ሥርዓት የተሰጠው አምነው ለዳኑ አማኞች በሙሉ ሲሆን ክርስቲያኖች ሁሉ ጌታን እንዲያስቡበት ጌታ አጥብቆ ይፈልጋል:: ይህ ማለት ግን አማኞች ለመታሰቢያው ያላቸው ክብር ዝቅ እንዳይል ሊጠነቀቁ ይገባቸዋል:: ከዚህም የተነሣ አማኞችን እንጀራውን እንዳይቆርሱ ሊያግዷቸው የሚችሉ ነገሮች መኖራቸውን ማወቅ ጠቃሚ ነው::

## እንጀራውን ከመቁረስ የሚያግዱ ሁኔታዎች

የጌታ ራት የብሉይ /አሮጌ/ ኪዳኑን የፋሲካ በዓል ተክቶ ለቤተክርስቲያን የተሰጠ ሥርዓት ነው:: በብሉይ ኪዳኑ የፋሲካ በዓል በጥላነት የተገለጹና አማኙን እንዲጠነቀቅ የሚያስተምሩ ነገሮች ተገልጸዋል::

**1. ከእርሾ አለመጠበቅ ከጌታ ራት ያግደናል**

በአሮጌው ኪዳን ዘመን ፋሲካን ለማክበር የሚፈልጉ ሰዎች በሙሉ በዓሉ ከመድረሱ አስቀድሞ 7 ቀናት ሙሉ (1 ሳምንት) በቤታቸው ውስጥ እርሾ እንዳይገኝ እግዚአብሔር አስጠንቅቆ ነበር:: **ዘፀ 12:14-20**

**➷ በአዲስ ኪዳን የእርሾ ትርጉም:-**

**ሀ. የተሳሳተ ትምህርት**

*ከማናቸውም ቅንጣት ታክል ስህተት /ዓመጽ/ ካለበት ትምህርት ሳምንቱን በሙሉ ራስን መጠበቅ ያስፈልጋል::* **ማቴ 16:6,12, 1ዮሐ 4:1-3, 2ዮሐ ቁ 9, 2ጢሞ 2:19::** *ያለበለዚያ ጥቂቱ እርሾ ብዙውን ሊጥ ያቦካልና ከእግዚአብሔር እውነት ሊያርቀንና ከተወደደው የጌታ ማዕድ ሊያግደን ይችላል::*

**ለ. የከፉ የሥነ-ምግባር /ኃጢአት/ ችግሮች ወይም የተገለጡ ኃጢአቶች::**

*መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉም የሰው ዘሮች ያለልዩነት ኃጢአተኞች እንደሆኑ ይገልፃል:: ለዚህ መፍትሔ ይሆን ዘንድም ኢየሱስ ለኃጢአተኞች ሞቷል:: አንድ አማኝ አምኖ ከዳነ በኋላ ግን በጣም በተገለጡ እና የሕይወት ምስክርነቱን በሚያበላሹ ጉዳዮች ከተጠላለፈ ይህ የክፋት እርሾ ፋሲካን እንዳያከብር/የጌታ ራትን እንዳይቆርስ ያደርገዋል::* **1ቆሮ 5:13, 1ጢሞ 5:24**

## መፍትሔ

*አማኞች የጌታ ራትን ከመቁረሳቸው በፊት ራሳቸውን በጥሞና መንፈስ ሊመረምሩና ሊናዘዙ በራሳቸውም ላይ ሊፈርዱ እና ምህረት ሊለምኑ ይገባቸዋል:: በራሳችን ላይ ቀድመን ከፈረድን ጌታ አይፈርድብንም ከዚህ በኋላ አማኙ እንጀራውን መቁረስ ይችላል::* **1ቆሮ 11:27-32**

## ፍርድ

*ወንድማችን ለመታሰቢያነት የሰጠንን ፎቅግራፍ አግባብ ባልሆነ ሥፍራ ብናስቀምጠው ወይም ትኩረት ሳንሰጠው ብንጥለው ይህ በቀጥታ ለእርሱ የነበረንን ክብርና ፍቅር እንደቀነስን ያሳያል::*

*ጌታ ለመታሰቢያነት የሰጠውን ይህን ሥርዓት የሚያናንቅ ወይም ክብር ባለመሥጠት ዓላማ እንደሌለው ተራ የምግብ ዳቦ እና ጽዋ ቆጥሮት ቢበላው ወይም ቢጠጣው የጌታን ሥጋ ምሳሌ ስለማይለይ እንዲሁም ደሙን ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላል::*

በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ በራሳቸው ላይ ሳይፈርዱ/ምህረት ሳይጠይቁ/ እንዲሁም ዓላማውን ባለመረዳት በእንጀራነቱና በጽዋነቱ ብቻ የበሉና የጠጡ ሰዎች በድካም፣ በበሽታ፣ እና በእንቅልፍ/ሞት/ ተቀጥተው ነበር:: **1ቆሮ 11:30**

## *የጌታ ራት "ጊዜ"*

ከሳምንቱ በመጀመሪያ ቀን /Sunday እሁድ/

እንጀራ ለመቁረስ ተሰብስበን ሳለን ... **ሐዋ 20:7** የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን /እሁድ/ ለጌታ ራት ሥርዓት ይሰበሰቡ ነበር:: ስለዚህ ለእግዚአብሔር ቃል በፍርሃት ለምትታዘዝ ቤተክርስቲያን ይህ ሳምንታዊና ቀጣይ የሆነ የተወደደ ሥርዓት ነው::

## ፀሎት (አምልኮት) ቃል ንባብ ወዘተ

በጌታ ራት ሥርዓት ላይ ሌሎች ምድራዊና ሥጋዊ እንዲሁም የኑሮ ጉዳዮች በርዕስነት አይነሱም:: ለነዚህ የራሳቸው የሆነ የፀሎት ኘሮግራም አላቸው:: በጌታ ራት ጊዜ አማኞች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር በመሆን መንፈስ እንደመራቸው የጌታን ሞት፣ መከራ፣ የማስታረቅ ሥራ ወዘተ የሚመለከቱ ዝማሬዎችን፣ ፀሎቶችን ያቀርባሉ:: እንዲሁም ተጓዳኝ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይነበባሉ:: ከዚያም እንጀራውን በመቁረስ ይካፈላሉ፣ ከጽዋውም ይጠጣሉ:: በመቀጠልም ለአብ የሚሆኑ ውዳሴዎችን በኢየሱስ ያቀርባሉ::

**"ኢየሱስ ብቻ ያድናል"**

## ማስታወሻ

የጥምቀትም ይሁን የጌታ ራት ሥርዓቶች **ለመዳን የተሰጡ** ሳይሆኑ **ለዳነ ሰው** ብቻ የተሰጡ ሥርዓቶች ናቸው:: ከዘላለም ሕይወት /መዳን/ ጋር ፈጽሞ ግንኙነት የላቸውም::

# ***ክፍል አራት***

## ***ፀጋ እና ሕግ***

- ኃጢአት አይገዛችሁምና ከፀጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና፡፡ **ሮሜ 6:14**
- ሕግና፣ ፀጋ በተለያዩ መጠሪያዎች ተነፃጽረዋል፡፡

| ***ሕግ*** | ***ፀጋ*** |
|---|---|
| 1. የኃጢአትና የሞት ሕግ | የሕይወት መንፈስ ሕግ **ሮሜ 8:2** |
| 2. አሮጌው የፊደል ኑሮ | አዲሱ የመንፈስ ኑሮ **ሮሜ** 7:6 |
| 3. በድንጋይ ላይ በፊደል የተፃፈ | በመንፈስ በልብ ፅላት ላይ **2ቆሮ 3:1-18** |
| 4. የሞት አገልግሎት | የመንፈስ አገልግሎት **2ቆሮ 3:7** |
| 5. የኩነኔ አገልግሎት | የጽድቅ አገልግሎት **2ቆሮ 3:7-11** |
| 6. አጋር /ብሉይ ኪዳን/ | ሳራ /አዲስ ኪዳን/ **ገላ 4:21-31** |
| 7. የሰዎች ጽድቅ | የእግዚአብሔር ጽድቅ **ሮሜ 3:21, 10:3, ኤፌ 2:18** |
| 8. የሥራ የሆነ ጽድቅ | የእምነት የሆነ ጽድቅ **ሮሜ 9:30-33 ሮሜ10:5-13** |
| 9. ሞግዚት | ክርስቶስ/እምነት/ **ገላ 3:21-29** |
| 10. የምትደክም /የማትጠቅም/ | የተሻለ ተስፋ **ዕብ 7:18** |
| 11. ፊተኛው /ብሉይ ኪዳን/ | ሁለተኛው /አዲስ ኪዳን/ **ዕብ 8:6-13** |
| 12. የናቀው ሞት ይገባዋል | ይልቅ የሚብስ ቅጣት ይገባዋል **ዕብ 10:28** |
| 13. በሙሴ ተሰጥቶ <u>ነበር</u> | በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ **ዮሐ 1:17** |

## ***ሕግ ለምን ተሰጠ?***

- ሰው ቢያደርገው ኖሮ በሕይወት እንዲኖር **ሕዝ 20:10, ገላ 3:12**
- በደል እንዲበዛ ሮሜ 5:21
- ኃጢያት እንዲታወቅ ሮሜ 7:7

ነገር ግን

1. በሕግ መጽሐፍት በተፃፈው ሁሉ ፀንቶ የማይኖር/አንድ ቀን የሚስት/ ሕጉን ሁሉ የማያደርገው የተረገመ ይሆናል፡፡ **ገላ 3:10**
2. ሁሉን ጠብቆ ነገር ግን አንዲቷን ቢተላለፍ በሁሉ በደለኛ ይሆናል፡፡ **ያዕ 2:10**
3. ይህም ቢሆን እንኳ ሕጉ የተሰጠው ለእሥራኤል ሕዝብ ብቻ ነበር፡፡ **ሮሜ 9:4**

- ይህም ስለሆነ ደግሞ

  - ሥጋ የለበሰ ሁሉ ሕግን ሙሉ በሙሉ መፈፀም አይችልም:: **ሮሜ 3:20**
  - በእግዚአብሔር ፊት ፃድቅ መሆን አይቻልም:: **ኢዮ 4:17, 9:2**
  - ተወልዶ እስኪሞት ሰው ጽድቅን ብቻ ማድረግ አይችልም:: **መዝ 13:2**
  - አንድ ስንኳ ፃድቅ የለም **መዝ 13:2, ሮሜ 3:11**
  - ፃድቅ የሚባል እንኳ ኃጢአትን ያደርጋል:: **መክ 7:20**
  - የሕግን ሥራ በመሥራት መጽደቅ አይቻልም **ሮሜ 3:20, 3:27, 4:2, 7:14, 6:14, ገላ 2:16, 3:10, 3:21, 4:21, 5:4, ኤፌ 2:8**

## «ፀጋ»

"ፀጋ" ማለት ለማይገባው ማንነት የተሰጠ ስጦታ ማለት ነው:: ይህም እንዲሁ በእግዚአብሔር ደግነት ላይ ተመስርቶ ኃጢአተኛ ለሆነው ሰው ያለምንም ምክንያት ከእግዚአብሔር ከፍቅር የተነሳ ብቻ የሚሰጠው ስጦታ ነው::

ፀጋና፣ ስጦታ ሁለት የተለያዩ ትርጉም ያዘሉ ቃላት ናቸው:: ስጦታ ከእኛ ጋር መልካም ወዳጅነት ላለው ሰው የምንሰጠውን መታሰቢያ የሚያካትት ሲሆን ፀጋ ግን ለሚጠላንና ክፉ ለሆነብን ሰው እንዲሁ ወደነው የምናደርግለት ስጦታ ነው:: እንግዲህ የፀጋ ስጦታ ማለት ሰውየው ከራሱ ተገቢነት የሚቀበለው ሳይሆን እንዲሁ የተሰጠው ነው ማለት ነው::

በዚህ መሠረት የዛሬ 2000 ዓመት የእግዚአብሔር ፀጋ ይኸውም በሕግ ሥራ ሊጸድቅ ያልቻለውን ሰው የሚያድን የእርሱ ፀጋ ተገልጧል:: ይህም ፀጋ ሰዎችን ሁሉ ማዳን ይችላል:: ነገር ግን ሰው ለመዳን ከፈለገ የግድ ይህንን ፀጋ በእምነት መቀበል ይኖርበታል:: **ቲቶ 2:11**

- ሰው የሚድነው ሕግን በመፈጸም ሳይሆን ፀጋውን በእምነት በመቀበል ብቻ ነው:: **ሮሜ 3:28**
- ኢየሱስ ፀጋንና እውነትን ተመልቶ መጥቷል **ዮሐ 1:14**
- ይህ ፀጋ ዓለምን ሁሉ ያድናል **ቲቶ 2:11**
- ፀጋው የሚያድነን ኢየሱስ ሥራችንን ሁሉ እንደሠራልን፣ ሕጉ ከእኛ የሚጠይቀውን እርሱ እንደፈጸመው በማመን፣ እንዲሁም በእኛ ሳይሆን በእርሱ ሥራ ወደ እግዚአብሔር እንዳቀረበን በማመንና በመቀበል ነው:: **ኤፌ 2:4-8, 2:18**
- የእግዚአብሔር ጽድቅ እንጂ የሰው ጽድቅ አያድንም **ሮሜ 3:21**

- እንዲያው መዳን /ያለምንም እኔነት/ **ሮሜ 3:21-28**
- ኃጢአተኛን እንደሚያጸድቅ ማመን ጽድቅ ሆኖ ይቆጠራል **ሮሜ 4:4-8, ሮሜ 4:9-25**
- ኃጢአታችን በጣም ብዙ ቢሆንም የወረደው ፀጋ ግን ከኃጢአታችንና ከበደላችን ሁሉ በጣም ይበዛል **ሮሜ 5:15-21, ሮሜ 4:9-25**
- በሕግ እንዳንጠየቅ ለሕግ ሞተናል **ሮሜ 7:1-6**
- በእምነት እንጂ በሥራ አይደለም **ሮሜ 9:30, 10:3-13**

**ተጨማሪ 2ቆሮ 3:4-17, 2ቆሮ 4:1-6, ገላ 2:16-21, ገላ 3:21-29, ቈላስ 2:16-23, ገላ 3:6-14**

- እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን ሰላምን እንያዝ **ሮሜ 5:1-11**
- ፀጋው ኃጢአተኛውን አድኖ ብቻ አያበቃም:: በዳነው አማኝ ውስጥ ሌሎች ተከታታይ ሥራዎችን ይሠራል:: አማኙ ራሱ እስኪደነቅ ድረስ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በአማኙ ሕይወት ውስጥ ልዩ ልዩ ሥራዎችን በመሥራት ባለብዙ ፍሬ ያደርገዋል:: **ቲቶ 2:11-15**
    - ይኸው ፀጋ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊ ምኞትን በማስካድ እውነተኛ የቅድስና ሕይወት እንድንኖር ያስተምረናል::
    - **2ቆሮ 4:13-15, 2ቆሮ 6:1-10** - በዚህ ውስጥ እያለፍን ወንጌልን መናገር ያስችለናል::
    - ጌታም ለዚህ የፀጋ ቃል የታመነ ነው:: **ቲቶ 3:3-7**

# አሜን::